# ወሲባዊ ትንኮሳ

## ግንዛቤ መፍጠር እና መከላከል ላይ ያተኮረ መመሪያ

Strategic Initiative
for Women in the
Horn of Africa

SIHA Network



# ወሲባዊ ጥቃት



ማንኛውም ያልተፈለገ ወይም በማስገደድ የሚደረግ የወሲባዊ ግንኙነት ወይም ባህሪ ሲሆን አስገድዶ መድፈርን፣ የአስገድዶ መድፈር ሙከራን እና ያልተፈለገ መንካትን ወይም መዳበስን ይጨምራል።

© SIHA Network



# ዓለምአቀፋዊ ሁኔታ



በዓለማችን ውስጥ ከ3 ሴቶች መካከል አንዷ ሴት በሕይወቷ በሆነ ወቅት ወሲባዊ ጥቃት ይደርስባታል።

© SIHA Network

**በአፍሪካ** ውስጥ የወሲብ ጥቃት መስፋፋት በሚያስደነግጥ ሁኔታ ከፍተኛ ነው። ለምሳሌ፡- **ከሰሃራ በታች ባሉ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ** ካሉ ሴቶች 45% የሚሆኑት በቅርብ አጋሮቻቸው አካላዊ ወይም ወሲባዊ ጥቃት እንደደረሰባቸው ሪፖርት አድርገዋል። የግጭት ቀጠናዎች ውስጥም ወሲባዊ ጥቃት እና አስገድዶ መድፈር በሰፊ ሁኔታ ይከሰታል።

© SIHA Network



# የወሲባዊ ጥቃት ዓይነቶች



ወሲባዊ ጥቃት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤ ነገርግን በእነዚህ ብቻ አይወሰንም፡-

- **አስገድዶ መድፈር፡-** በኃይል ወይም በግዳጅ የሚፈጸም የግብረ ሥጋ ግንኙነት
- **ትንኮሳ፡-** የማይፈለጉ ወሲባዊ ሙከራዎች ወይም አስተያየቶች
- **አካላዊ የሆኑ ወሲባዊ ንክኪዎች፡-** አግባብ ባልሆነ መልኩ መንካት ወይም መዳበስ
- **በልጆች ላይ የሚፈጸም ወሲባዊ ጥቃት፡-** ለአካለ-መጠን ካልደረሰ/ካልደረሰች ልጅ ጋር የሚደረግ ማንኛውም አይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት

© SIHA Network

# መቼቶች / አውዶች

ወሲባዊ ጥቃት በተለያዩ ሁኔታዎች ወይም መቼቶች ውስጥ ሊከሰት ይችላል። ከእነዚህም ውስጥ፡-


- **ቤት ውስጥ**
- **በሕዝብ ቦታዎች** (ለምሳሌ፡- በመንገድ ላይ፣ በመናፈሻዎች ውስጥ፣ በገበያ ሥፍራ፣ ወዘተ)
- **የሥራ ቦታ**
- **ግጭት ያለባቸው ቀጠናዎች ውስጥ**
- **ትምህርት ቤቶች እና በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ**
- **በበይነ-መረብ (ኢንተርኔት) መድረኮች**

© SIHA Network



# ጥቃት ሊያደርሱ የሚችሉ ሰዎች

ወሲባዊ ጥቃት ብዙ ጊዜ የሚፈጸመው ጥቃት የደረሰበት ሰው በሚያውቀው ሰው ነው። ከእነዚህም ውስጥ፡-



**የቅርብ አጋሮች**
(ባሎች፣ የፍቅር ጓደኞች፣ የትዳር አጋሮች)



**ጓደኞች ወይም የሚታወቁ ሰዎች** (የሥራ ባልደረቦች፣ የክፍል ጓደኞች)



**የቤተሰብ አባላት**
(አባቶች፣ አጎቶች፣ ወንድሞች)



**እንግዳዎች ወይም የማይታወቁ ሰዎች**
(ብዙ የተለመደ ባይሆንም በአደባባይ ወይም ሰዎች በሌሉባቸው ቦታዎች)

© SIHA Network



# ጥቃት በደረሰባቸው ሰዎች ላይ የሚደርሱ ተጽዕኖዎች



**ወሲባዊ ጥቃት በደረሰባቸው ሰዎች ላይ ከባድ ተጽዕኖ ይደርሳል፤ ይህም የሚከተሉትን ያካትታል፡-**

- በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ ኢንፌክሽኖች፣ ያልተፈለገ እርግዝና፣ የአካል ጉዳት እና ሌሎች ተመሳሳይ የአካላዊ ጤና ችግሮች
- አንዳች አደጋን ወይም ዘግናኝ ጥቃትን ተከትሎ የሚከሰት የአእምሮ ሁከት (PTSD)፣ ጭንቀት፣ ድብርት፣ ወይም ራስን ማጥፋትን ጨምሮ የሥነ-ልቦና ጉዳቶች (ቁስለቶች)
- ማኅበራዊ መገለል እና ማግለል - በተፈጠረው ክስተት ምክንያት የአንድ ሰው ሥራ እና ማኅበራዊ ሕይወት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል።
- ሥር የሰደዱ አካላዊ እና ሥነ-ልቦናዊ የጤና ችግሮች
- ሌሎች ሰዎችን ለማመን እና ጤናማ ግንኙነት ለመመስረት መቸገር

© SIHA Network

# እንዴት መከላከል ይቻላል?

ወሲባዊ ጥቃትን የመከላከያ ዘዴዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

በፍቃድ እና በመከባበር ላይ የተመሠረቱ ግንኙነቶች ላይ ግንዛቤ መፍጠር

ሀብት (እገዛ)፣ ድጋፍ እና ደህንነታቸው የተጠበቁ ቦታዎችን በመስጠት ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎችን ማበረታታት

ጠንካራ የሕግ ማዕቀፎችን መዘርጋት እና ወሲባዊ ጥቃት ላይ የወጡ ህጎች ተፈጻሚነትን ማረጋገጥ

ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎችን ተወቃሽነት ለመቀነስ እና ደጋፊ የሆነ ሁኔታን ለመፍጠር የማኅበረሰብ ተሳትፎ ዘመቻዎችን ማካሄድ

© SIHA Network

# በመከላከል ላይ የሁላችንም ሚና





**ግለሰቦች፦** የሰዎችን ግላዊ ድንበሮች መገንዘብ እና ማክበር፣ ተገቢ ያልሆነ ባህሪይ ሲመለከቱ ደፍሮ መናገር፣ ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎችን መደገፍ



**ማኅበረሰቦች፦ የመከባበር እና የእኩልነት ባህል መፍጠር፣ በወሲባዊ ጥቃት ላይ ግልጽ ውይይቶችን ማበረታታት**



**መንግስታት፣ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች እና የልማት አጋሮች፦** ወሲባዊ ትንኮሳን ለመከላከል እና ጥቃት የደረሰባቸው ሰዎችን ለመደገፍ የሚያስችሉ ሕጎች እና ፖሊሲዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ

© SIHA Network